የሰ/መ/ቁ. 41767

ኀዳር 8 ቀን 2002 ዓ.ም

**ዳኞች**፡- መንበረፀሐይ ታደሰ

ሐጐስ ወልዱ

ሒሩት መለሰ

አልማው ወሌ

ዓሊ መሐመድ

**አመልካች**፡- የአዲስ አበባ ውሃና ፍሳሽ ባለሥልጣን ነ/ፈጅ ተካ ገ/መድህን ቀረቡ

**ተጠሪ**፡- አቶ አድማስ ደምሳቸው የቀረበ የለም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

## ፍ ር ድ

ጉዳዩ የአሰሪና ሰራተኛ አዋጅን መሰረት ያደረገ ሲሆን ክርክሩ የተጀመረው የአሁኑ ተጠሪ ታህሣሥ 15 ቀን 2000 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የክስ ማመልከቻ ከጥር 25 ቀን 1997 ዓ.ም ጀምሮ ለአመልካች በጉዳይ አስፈፃሚነት ሲያገለግሉ መቆየታቸውን ገልፀው ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት ሳይኖር ወይም ቢኖርም እንኳ ከታወቀ ከአንድ ወር በኂላ ያሰናበታቸው በመሆኑ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ ወደ ስራ እንዲመለሱ ወይም የተለያዩ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እና የስራ ልምድ ምስክር ወረቀት ተሰጥቷቸው እንዲሰናበቱ በጠየቁት ክስ መነሻ ነው፡፡ የአሁኑ አመልካችም በተከሳሽነቱ ቀርቦ በሰጠው መልስ ስንብቱ የተፈፀመው ተጠሪ ሌላ ቦታ በመስራታቸው መሆኑንና ይህንንም እንደአወቀ የስንብቱ እርምጃ መፈፀሙን በመግለጽ ተከራክሯል፡፡ ፍርድ ቤቱም የግራ ቀኙን የጽሑፍ ክርክር ከመረመረ በኂላ አመልካች ተጠሪን ባሰናበተበት ጊዜ በቂ እና ሕጋዊ ምክንያት ያልነበረው መሆኑን በመግለጽ ስንብቱ ከሕግ ውጪ ነው በሚል ምክንያት ተጠሪ የስድስት ወር ደመወዝ ተከፍሏቸው ወደ ስራቸው ሊመለሱ ይገባል፣መመለስ ካልፈለጉ ተገቢ ክፍያዎች ተከፍሏቸው እንዲሰናበቱ ይደረግ ሲል ወስኗል፡፡ በዚህ ውሳኔ የአሁኑ አመልካች ባለመስማማት ይግባኙን ለፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቦ ግራ ቀኙ ከተከራከሩ በኂላ ስንብቱ የተፈፀመው ለስንብቱ ምክንያት የሆነው ድርጊት ከተፈፀመ ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኂላ በመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ በይርጋ ይታገዳል፣የአመት እረፍት የሁለት ዓመቱ ለተጠሪ ሊከፈላቸው አይገባም ሲል ምክንያቱን ለውጦ የስር ፍ/ቤትን ውሣኔ በማሻሻል ወስኗል፡፡ የአሁኑ የሰበር አቤቱታ የቀረበውም ይህንኑ ውሳኔ ለማስቀየር ነው፡፡

የአመልካች ነገረ ፈጅ ኀዳር 30 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሦስት ገጽ የሰበር ማመልከቻ በስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ ላይ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሉበትን ምክንያት ዘርዝረው አቅርበዋል፡፡ ይዘቱም፡- ስንብቱ ጊዜውን ጠብቆ የተደረገ አይደለም ተብሎ ሕገ-ወጥ ነው መባሉ በጉዳዩ ላይ የቀረበውን ማስረጃ ባግባቡ ባለመመልከቱና ጊዜ አቆጣጠሩም ግልጽነት በሌለው ሁኔታ ተሰልቶ በመሆኑ ውሳኔው ሊታረም ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው ተመርምሮም በሰበር ችሎቱ ሊታይ ይገባዋል በመባሉ ተጠሪ ቀርበው ሰኔ 18 ቀን 2001 ዓ.ም በተፃፈ ሁለት ገጽ ማመልከቻ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡ ይዘቱም ባጭሩ፡- አመልካች ተጠሪን በመጀመሪያ ከሥራ ያሰናበተበት ምክንያቱን ተመርኩዞ ለስንብት የሚያበቃ ምክንያት የለም ተብሎ እና በተጨማሪም የስንብት ምክንያቱ በይርጋ ይታገዳል ተብሎ የተሰጠው ውሣኔ መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት የሌለው በመሆኑ ሊፀና ይገባል በማለት መከራከራቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ በበኩላቸው ሐምሌ 24 ቀን 2001 ዓ.ም በፃፉት ማመልከቻ የሰበር አቤቱታቸውን በማጠናከር የመልስ መልሳቸውን ሰጥተዋል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ አጠር ባለመልኩ ከላይ የተገለፀው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሣኔ እና አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች ጋር በማገናዘብ በሚከተለው መልኩ መርምሮታል፡፡

እንደመረመርነው አመልካች የተጠሪን የሥራ ውል ያቋረጠው በአዋጁ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/3/ መሰረት በሰላሳ የስራ ቀናት ውስጥ አይደለም ተብሎ ስንብቱ ሕገ-ወጥ ነው ተብሎ መወሰኑ ባግባቡ መሆን ያለመሆኑ በጭብጥነት ሊታይ የሚገባው ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ከክርክሩ መገንዘብ የተቻለው ተጠሪ የአመልካች መስሪያ ቤት ሰራተኛ ሆነው በሚሰሩበት ወቅት በሌላ ቦታ መስራቱ ሲታወቅ አመልካች የስራ ውሉን በማቋረጥ ያሰናበታቸው መሆኑንና ተጠሪም ይህንኑ ፍሬ ነገር ሳይክዱ የሚከራከሩት ስንብቱ የተፈፀመው ሰላሳ የስራ ቀናት ከአለፉ በኂላ ነው በሚል መሆኑን ነው፡፡ ተጠሪም ሆነ የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት አመልካች የድርጊቱን መፈፀም ያወቀበት ጊዜ በማለት የሚቀበሉት ነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ሲሆን የስንብት ደብዳቤ ተሰጠ የሚባለው ደግሞ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ነው፡፡ የአመልካች ነገረ ፈጅ አጥብቀው የሚከራከሩት ይህ ጊዜ ቢያዝ እንኳ የሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ አላለፈም በማለት ነው፡፡ እኛም ይህንኑ መሰረት በማድረግ ጊዜውን ስናሰላው ከነሐሴ 16 ቀን 1999 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጳጉሜ 06 ቀን 1999 ዓ.ም ድረስ አስራ አምስት፣ከመስከረም 01 ቀን 2000 ዓ.ም ጀምሮ የስንብት ደብዳቤ አስከተፃፈበት እስከ መስከረም 21 ቀን 2000 ዓ.ም ድረስ ደግሞ 13 ተከታታይ የስራ ቀናት መኖራቸውን አረጋግጠናል እነዚህ ቀናት በጠቅላላው 28 ናቸው በአዋጅ ቁ.377/96 አንቀጽ 27/3 መሰረት አንድ አሰሪ ህጉ በተፈቀደው ምክንያት መሰረት የሥራ ውሉን የሚያቋርጥበት ጊዜ የስራ ውሉ የሚቋረጥበት ምክንያት መከሰቱ ካወቀበት ከሰላሣ የስራ ቀናት በኂላ ከሆነ በይርጋ እንደሚታገድበት ተደንግጓል፡፡ በተያዘው ጉዳይ ግን ከላይ እንደተመለከተው ሰላሳ ተከታታይ የሥራ ቀናት ከማለፋቸው በፊት አመልካች እርምጃውን ወስዷል፡፡ በመሆኑም የከፍተኛው ፍርድ ቤት ድምዳሜ ጊዜውን በተመለከተ ካላንደሩን ባግባቡ ያላገናዘበ በመሆኑ ስህተት ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ስለሆነም የአመልካች እርምጃ በሰላሳ ቀናት የጊዜ ገደብ የሚታገድበትን ህጋዊ ምክንያት አላገኘንም፡፡ ስንብቱ መሰረት ያደረገበትን ምክንያት በቂ መሆን ያለመሆኑን ስንመለከተው ተጠሪ አመልካች የማታለል ተግባር ፈጽሚል በማለት የሚያቀረበውን ክርክር ጉዳዩን አመልካች ያውቅ ነበር ከማለት ውጪ ድርጊቱ መፈፀሙን የካዱት ነጥብ አይደለም፡፡ አንድ ሰራተኛ በአሰሪው ላይ የማታለል ተግባር መፈጸሙ ከተረጋገጠ አሰሪው የሥራ ውሉን ያለማስጠንቀቂያ ለማቋረጥ ሕጋዊ መብት ያለው መሆኑን አዋጅ ቁጥር 377/96 አንቀጽ 27/1/ሐ/ ድንጋጌ ያስገነዝባል፡፡ አሰሪ ግልጽ የሆነ ፈቃድ እስካልሰጠ ድረስ ሰራተኛው በሁለት ቦታ በተመሳሳይ ጊዜ መስራቱ ከታወቀ አድራጎቱ በስራ ላይ የተፈፀመ የማታለል ተግባር ነው ከሚባል በስተቀር ሌላ ትርጉም የሚሰጠው አይሆንም፡፡ በምርትና ምርታማነት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያስከትል በመሆኑ የስራ ውሉን ለማቋረጥ ሕጋዊ እና በቂ ምክንያት ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ተከታዩን ወስነናል፡፡

## ው ሳ ኔ

1. የፌዴራሉ መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 39185 ሰኔ 13 ቀን 2000 ዓ.ም ተሰጠቶ በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁጥር 68366 ኀዳር 22 ቀን 2001 ዓ.ም የፀናው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ. 348/1/ መሰረት ተሽሯል፡፡
2. አመልካች ተጠሪን ከስራ ያሰናበተው በሕጉ አግባብ ነው ብለናል፡፡
3. ለክርክሩ የወጣውን ወጪና ኪሣራ የየራሣቸውን ይቻሉ ብለናል፡፡

መዝገቡ ተዘግቷል፤ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ቤ/ኃ